# ከ1500 በላይ ኢትዮጵያዊያን በየመን እስር ቤት ይሰቃያሉ

ከግሩም ተክለሃይማኖት

ከ1500 በላይ ኢትዮጵያዊያን በሱማሊያ አድርገው በባህር ወደ የመን የገቡ ስደተኞች በተለያየ ከተማና እስር ቤቶች ውስጥ ይሰቃያሉ:: በአረብኛው ጀዋዛት የሚባለው /ሰነዓ ሚግሬሽን እስር ቤት/ 631 እስርኞች እንዳሉ በዛሬው እለት /እርብ ታህሳሰ 23፣ 2003 ዓ. ም. አረጋግጠናል:: በዋናው እስር ቤት /በእነሱ አጠራር መርከዚ የሚሉት ቦታ/ ባለፈው ዘገባዬ ካቀረብኳችው ወደ 800 የሚጠጉ እስረኞቸ በተጨማሪ ከ250 በላይ የተቀላቀሉ ቢኖሩም በእርግጠኝነት ምን ያህል እንደተጨመሩ መረጃ ለማግኘት ያረኩት ጥረት አልተሳካም:: ይህ የእስረኛ ብዛት በሰሜናዊ የመን ከሳዑዲ አረቢያ ተባረው በችግር ያሉትን ወደ 1200 የሚጠጉ ስደተኞችን አይጨምርም::



*"ይህ ጀልባ በምን አይነት ሁኔታ እንደጫነ ልብ በሉ:: በጣም አነስተኛ ከ28 ስው በላይ መጫን የማይችል፣ በሀገራችን ለምሳሌ በባህርዳር፣ በአዋሳ ... የመሳሰሉት አካባቢ የሚጠቀሙበት አይነት ነው:: አሁን የጫነው ግን 157 ስው ነው:: ከላይ ከፍ ብሎ የምታዩት ፓርት ከስሩም ሰው ተጠቅጥቋል:: እንደዚህ ተጭነው ከ36 እስከ 41 ሰዓት ይጓዛሉ። ሱማሊያ ውስጥ ከሚያዩት ስቃይ ውጭ እዚህ ጀልባ ላይ ያለ ዱላ መፈጠርን ያስጠላል:: አንስተው ወደ ባህር ሁሉ ይወረውራሉ:: እኔም በዚህ ሁኔታ ተጉዤ እዚህ ነው የመን የደረስኩት እና የዘጠኝ ወር እርጉዝ ስትጓዝ ለማየት የቻልኩበት ሁኔታ አለ::"*

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጆሮ ዳባ ልበስ ያለበት ሁኔታ በጉልህ ይታያል:: የኢትዮጵያ ኮሙኒቲም ለስሙ የቆመ የካድሬዎች ጎሬ ከመሆኑ ባሻገር ለዜጎቸ የሚሰጠው ጥቅም አይታይም:: ጉዳት ደርሶባቸው ጎራ ያሉ ወገኖች ማረፊያ ባዶ ማጎሪያ ክፍል ከመስጠት ውጭ ምንም አያደርግም:: በትላንትናው እለት ጎራ ብየ ያናገርኳችው ችግረኞች የሚበሉት እንኳን ስው ካልሰጣቸው በረሀብ እንደሚሞቱ ምንም እንዳልተደረገላቸው ግልጸውልኛል::